# የሰአት ባትሪዎችን ልጆች በማይደርሱበት ቦታ ያኑሩ




**ልጅዎ የሰአት ባትሪዉን ከዋጠ፣ በምግብ ቧንቧው ውስጥ ገብቶ ሊያንቀው ይችላል፡፡ ዋናው የደም ወሳጅ ቧንቧ ሊቃጠልና ክፉኛ ሊጎዳቸው የሚችል ሲሆን ከዛም አልፎ ተርፎም ሊገድላቸው ይችላል፡፡ ይህም ሁኔታ በጣም በፍጥነት ሊከሰት ይችላል፡፡**

**እድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 4 አመት ½ የሆናቸው ሕጻናት ለዚህ አደጋ የተጋለጡ ናቸው፡፡**

## የትኞቹ የሰአት ባትሪዎች በጣም አደገኛ ናቸው?

የሊቲየም ሳንቲም ሴል ባትሪዎች ከ 5 ሳንቲም ትንሽ ከፍ ይላሉ፡፡ ለማነቅና ለመግደል በቂ ጥንካሬ አላቸው፡፡

አነስ ያሉ የሰአት ባትሪዎች በተለይ አዲስ ከሆኑ አሁንም ቢሆን ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡

## የት አሉ?

ልጅዎ እነዚህን በመሳሰሉት ነገሮች ላይ የሰአት ባትሪዎችን ሊያገኝ ይችላል፡

- ትናንሽ የርቀት መቆጣጠሪያዎች
- የመኪና ቁልፎች ወይም ቁልፍ መፈለጊያዎች
- የሙዚቃ ካርዶችና መጽሐፍት
- ቀለል ያሉ አሻንጉሊቶችና አዲስ እቃዎች
- የምሽት መብራቶች
- ዲጂታል ሚዛኖች
- ቴርሞሜትሮች
- ከአሮጌ አሻንጉሊቶች በአሻንጉሊት ሳጥን ውስጥ

ልጆች ሊደረስበት በሚችል ቦታ የተቀመጡ ወይም ከማሸጊያው አምልጠው የወደቁ ትርፍ ባትሪዎችን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

ኃይላቸውን ጨርሰው 'የሞቱ' ባትሪዎች እንኳን ቢሆኑም አደገኛ ሊያደርጋቸው የሚችል ያህል ቻርጅ ይይዛሉ፡፡

## በቤትዎ በሙላ ይፈልጉ

- የሰአት ባትሪዎች በቤትዎ በሙላ ይፈልጉ
- የባትሪው መያዣ ደህንነቱ ካልተጠበቀ እቃውን ልጅዎ የማይደርስበት ቦታ ያስቀምጡት
- ተቀያሪዎቹንና 'የሞቱትን' ባትሪዎችን እንዳይደረስባቸው አድርገው በደንብ ያስቀምጡ
- ከኦንላይን የገበያ ቦታዎች ወይም በአካባቢውዎ ከሚገኙ የቅናሽ ሱቆች ከሚኖር ግብይት ይጠንቀቁ፡፡ ልጅዎ በቀላሉ ሊያገኛቸው የሚችላቸው የሰአት ባትሪዎች ሊኖራቸው ይችላል፡፡

## ልጅዎ አንዱን ውጧል?

- **አይዘግዩ፡፡ በቀጥታ ወደ A&E ይውሰዷቸው ወይም አንቡላንስ ለመጥራት 999 ላይ ይደውሉ፡፡**
- **ልጅዎ የሰአት ባትሪ ሳይውጥ አይቀርም ብለው እንደሚያስቡ ለዶክተሩ ይንገሩ፡፡**
- **የባትሪው ማሸጊያ ወይም ባትሪው የወጣበት እቃ ካልዎት እሱንም ይዘውት ይሂዱ፡፡**
- **እንዲበሉ ወይም እንዲጠጡ አትፍቀዱላቸውና አያሳምሟቸው**

**የተወሰኑ ጥቂት ምልክቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ቀልብዎን የነገርዎትን ይመኑ፡፡**

capt.org.uk/button-batteries

@ChildAccidentPreventionTrust

child accident prevention trust